የካቲት 3ቀን 2000ዓ.ም (11-2- 2008)

# የልጆች የሰቀቀን ጩኸት

**ከአያልነሽ**

''ብሌን ታምራት እባላለሁ፡ የምጽፈዉም በመላ ቤተሰቡ ስም ነው። አባቴ የቀድሞ ጠቅላይ ሚንስትር ሲሆን እስር ቤት ከገባ 11 ዓመት አድርጓል። ካለ አባት ማደግ ግድ ሆኖብናል በተለይም(እሱ ሲታሰር) 2 ወር የነበራት ታናሽ እህቴ። እስርቤት በገባበት ዓመት ውስጥ ስለነበር የተወለደችው ጠቅላላ ሕይወቷን ሙሉ ከሱ ጋር ምንም ግንኙነት ሳያኖራት ነው ያሳለፈችው። መቼም ካላ አባት ማደግ ምን ያህል ከባድ ህመም እንደሆነ ልገልጸው አልችልም።''

ይህን ከዚህ በላይ የሰፈረውን ክፍት ደብዳቤ ብላ ልብ የሚሰብር መልዕክት የጻፈችው፤ ብሌን ታምራት ስትሆን ደብዳቤውን የጻፈችው ለመለስ ዜናዊ ነው። ብሌን ወላጅ አባቷ የሆነው ታምራት ላይኔ፣ በወያኔ አገዛዝ ለእሥር ተዳርጎ ዘብጥያ ከወረደ ከ11 ዓመት በላይ አስቆጥሯል። የብሌን አባት ታምራት ላይኔ በአሰረው አገዛዝ ውስጥ፣ የአገዛዙ ሹመኛ የነበረ ሲሆን፣ የአገዛዙ ጎራዴ ባለ ሁለት አፍ (ስለት) ነውና የአገዛዙን አሽከሮች ሁሉ ሳይቀር፣ ከመቅላት አልተቆጠበም። በዚሁ ሳቢያ አቶ ታምራት ላይኔ የዚሁ ጎራዴ ሰለባ ሆኗል። የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ እንደማንኛውም አምባገነናዊ አገዛዝ ፈላጭ ቆራጭ በመሆኑ፣ በብዙሃኑ ጭቁን ሕዝብ ላይ እንዲያርፍ አድርጎ የሳለው ጎራዴ፣ የአገዛዙንም ቤት አንድ በአንድ እየነካካ ማለፉ አይቀሬ ነው። በመንግስቱ ኃ/ማርያም አገዛዝ ወቅትም ይህ ክስተት ታይቷል። የመንግሥቱ አገዛዝ ያኔ እነ አጥናፉ አባተንና እነ ተፈሪ በንቲን የመጀመሪያው የሰይፉ መሳያ አድርጎ ሲቀላ፤ የፍየል ወጠጤን አጃቢ አድርጎ መሸኘቱ አይዘነጋም። ከዚያ ተከትሎ የመጣውን ጣጣ የትናንትና ትውስታችን ነውና ታሪክ መዝግቦታል። ለዚህም ነው የአምባገነን አገዛዞች ሰይፍ፣ ሁለት ስለት አለው የሚባለው። በጭቆናቸው ሥር የወደቀውን አብዛኛውን ጭቁን ሕዝብ እየቆራረጠ ለመሄድ ሲሞክር፣ የአገዛዙንም ሰዎች አብሮ እየቀላ ነው የሚያልፈው። የሚያሳዝነው ግን ይህ ጎራዴ ያረፈባቸው ሹመኞች፣ በእነርሱ ጠስ እነርሱን ብቻ ሳይሆን ቤተሰባቸውን ጭምር አብሮ መቆራረጡና ማስከፈሉ ነው። የብሌን የደብዳቤ መልዕክት ለሁላችንም የሚያስተላልፈው፣ እነሱን በማይመለከታቸውና በማያውቁት ጉዳይ የዚህ እዳ ተሸካሚና ተጋሪ መሆናቸው ነው። ስዬና ባልደረቦቹ ከእነ ብሌን ታምራት ምን ይማራሉ? እነ ስዬ ለልጆቻቸው የሚያውርሱትስ ይህንኑ ይሆን? ለምን? በቤተሰቦቻቸው በአጠቃላይ በልጆቻቸው ላይ በተለይ፣ ለሚደርስባችው የሥነ-ልቡና ችግር ተጠያቂው ማን ነው? ለምንስ ለልጆቻቸው ይሄን ኃጢዓትና እዳ ለማውረስ ይገደዳሉ/ይመኛሉ? ልጆችስ ያለ እዳቸው ይሄንን መክፈል አለባችው/ይገባቸዋልስ? እጅግ ዘግናኝና ልብ የሚሰብሩ ጉዳዮች። ይህንን ዓይነት የበደል በደል ነው እነ ስዬና ባልደረቦቹ፣ ለልጆቻቸው እንዳያወርሱና እንዳያስተላልፉ አደራ የምላቸውና የምማጸናቸው። እባካችሁ! አሁንም ቁልፉ ከእጃችሁ ውስጥ ነው እላችኋለሁ።

የተከበራችሁ አንባቢዎች ሆይ!

ልጆች ከመወለዳቸው በፊት መሰረታዊና አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ሊሟላላቸው ይገባል። ህጻናት ወንዶች ሆኑ ሴቶች፣ ከሀብታም ይወለዱ ከድሃ፣ የጥቁር ይሁኑ የነጭ፣ የትም ይወለዱ የት ከሁሉ በፊት የወላጆቻቸውን ፍቅርና ደስታ ሳይጓደል ማግኘት ይሻሉ። ወላጆቻቸው የሚሰጧቸው ፍቅር ምግባቸው ሆኖ ጤነኛ ሆነው እንዲያድጉ ይረዳቸዋል። ወላጆቻቸው የሚያሳዩዋቸው ደስታና ሳቅ ልጆችን ፍልቅልቅ ያደርጋቸዋል። ልጆች ከምንም በላይ ፍቅርን ይወዳሉ። ወላጆቻቸው የሚያሳዩቸው ደስታና ፍቅር ለልጆች ዋስትና ነው። ልጆች ከወላጆቻቸው የሚያገኙትን ፍቅር ምንም ያህል ገንዘብ አይተካውም። እነ ብሌን ዛሬ ያጡት በገንዘብ የማይተካውንና የማይሸፈነዉን የአባታቸውን ፍቅር ነው። እነ ብሌን ሁሌ ባዶነት ይሰማቸዋል፤ እንደ ልጆች አይስቁም፤ እንደ ልጆች አይደሰቱም፣ እንደ ልጆች ስሜታቸውን መግለጽ አይችሉም። እንደ ልጆች አባት አለን ብለው ደፍረው በኩራትና በአስተማማኝነት ለጓደኞቻቸው መንገር አይችሉም። ለነ ብሌን ሁሉ ነገር ተደፍቶባቸዋል። እስቲ እያንዳንዱ ወላጅ ለደቂቃ የአባት ወይ የእናት ፍቅር አጥተው የሚያድጉ ልጆችን፣ እንደራሳችን አድርገን በምናባችን እናስባቸውና፣ ስሜታችንን እናዳምጠው። ምን ተሰማን ይሆን? ያውም ያለ ጥፋታቸው እዳ የሚከፍሉ ልጆች።

ብሌን ታምራት ደብዳቤዋ ረዥም ነው። እኔ ግን ዋና ዋና መልዕክቶቿን ነው ለማስፈር የሞከርኩት። ከረዥሙ ደብዳቤዋ ውስጥ በቀጣዩ ላይ እንዲህ ትላለች

> "ሌሎች ልጆችን ከአባቶቻቸው ጋር ሆነው ሳይ ለኔ በጣም ከባድ ነው። እኔና እህቴ የአባታችን ድምጹ ምን እንደሚመስል እንኳን ማስታወስ እያቃተን ነው። ለረዥም ዓመታት ካለ አባታችን ማደግ ግድ ሆኖብናል። በጣም እንናፍቀዋለን። እህቴ 8 ዓመት ሲሆናት ነበር አባታችን እስር ቤት መሆኑን የነገርናት። እናም በጣም ነው የደነገጠችው፤ በጣም ነው የተጎዳችው። ከዚያ በኋላም ለሰዓታት አለቀሰች። በየቀኑም እንደምትናፍቀው (እንዳጎደለባት) ትነግረኝና መቼ እንደሚመጣም ትጠይቀኝ ጀመር። "

ብሌን ታምራት ደብዳቤዋ ሰፊ ነው፡ ይህንን ልብ የሚሰብር ደብዳቤ ትጻፍ እንጅ የብሌን ዓይነት እጣ ፈንታ ያጋጠማቸው፣ ያለ ወላጅ ያደጉ ህጻናትና ለዓቅመ አዳም ያልደረሱ ለጋ ለጋ ልጆች በኢትዮጵያችን ውስጥ ብዙ ናቸው። በወያኔ አገዛዝ በጥይት ተደብድበው ወላጆቻቸውን የተነጠቁና ያለ አባትና እናት የሚያድጉ ልጆችም ቁጥራቸው የትየለሌ ነው። የአቶ አበራ የማነአብ ልጅ ከህጻንነቱ ጀምሮ ያለ አባት ያደገና የአባት ፍቅር ረሃብተኛ ነው። የአቶ ተስፋዬ ታደሰ ልጆች አባታቸውን በወያኔ ጥይት ተንጥቀዋል። አቶ አስፋ ማሩም ልጆቻቸው አባት አልባ ናቸው፥..... በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲህ ዓይነት የወላጆቻቸውን ፍቅር ሳያገኙ የሚኖሩ ልጆች እጅግ ብዙ ናቸው። ያውም አምባገነኖች በሚሰሩትና በሚፈጥሩት ችግርና ጣጣ። ህጻናትና ልጆች ለዘመናት የሚያሰሙትን የሲቃ ጩኸታቸውን ስንቶቻችን ይሆን ያዳመጥነዉና የምናዳምጠው? የዕድሜ ልክ ሰቀቀን።

ብሌን ለመለስ ዜናዊ በላከቻው የተማጽኖ ደብዳቤዋ እንዲህ ትላለች

"እስቲ አንድ ጊዜ ልጆቻችሁ ያለ አባት ቢያድጉ የእናንተም የልጆቻችሁም ህይወት ምን ሊመስል/ሊሆን እንደሚችል አስቡት። ባለቤቷን በማጣቷ የምታነባ/የምታለቅስ እናታቸውን እያዩ የሚያድጉ ሊሰማቸው የሚችለውን አስቡት። ከስራ ስትመለሱ ልጆቻችሁን እንደምታቅፏቸውና እወድሃለሁ/እወድሻለሁ እንደምትሏቸው አውቃለሁ። እኛ ግን ይህ (ዕድል) የለንም። ልጆቻችሁን ማታ ማታ ለመኝታ ወደ አልጋቸው ከወሰዳችኋቸው በኋላ ከአልጋቸው አጠገብ ሆናችሁ አለሁልህ/አለሁልሽ አብሬሽ/ህ ነኝ እንደምትሏቸው አውቃለሁ። እኛ ግን ይሄ የለንም። እኔና እህቴ ገና ልጆች ነን፤ ግን ብዙ ተሰቃይተናል። ለምንስ ከለ አባት መኖር አለብን?
ለህይወታችን/ለዕድገታችን የሚወደን አባት ሊኖረን ይገባል/ያስፈልገናልም። እናንተ ልጆቻችሁን እንድምትወዱት ሁሉ እኛም የሚወድ፣ የሚንከባከብ አባት ሊኖረን ይገባል። ትልና በማስከተል

ይህንን ደብዳቤ የምጽፈው የእኔና የእህቴን እድገት እያየ፣ ፍቅሩን እየሰጠን የሚያሳድገን አባት እንዲኖረን እባክዎን! አባታችንን ይፍቱልን ብዬ ለመጠየቅ ነው።"' ብላ ሰቀቀኗን ለመለሰ ዜናዊ ትገልጣለች።

ብሌን እንደማንኛውም ልጅ አባቷ ከአጠገቧ አይደለምና ደብዳቤዋ አባቷ እንዲፈታላት በአጽንኦት የሚማጸንና የሚጠይቅ ይሁን እንጂ፣ ጥያቄው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሊጨነቅበትና ሁሉም የብሌንን ጩኸት ሊያስተጋባው የሚገባ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ሰው በፖለቲካ አስተሳሰቡ፣ አመለካከቱና አቋሙ ሳቢያ መታሰር፣ መገደል፣ መሰደድና መጋዝ የለበትም ብለን በመጮህና በመታገል፣ ለአንዴና ለሁሌ በሰዎች ላይ የሚደርሰውን ግፍ ማስቆም መቻል አለብን። ይህ ደግሞ መብት ብቻ ሳይሆን ሰብዓዊ ግዴታችንም መሆኑን ልንገነዘብና ልናሰምርበት ይገባል። በአንደኛው ላይ ስለደረሰ ወይ ስለተደረገ እኔ ጋ አልተደረገም ወይም እኔ ጋ አልደረሰም በሚል ፍጹም ኢ-ሰብዓዊ በሆነ አስተሳሰብ ኢ-ፍትኃዊ የሆነ ድርጊትን አልመቃወምና በዝምታ ማሳለፍ፣ ቢያንስ <u>የሰውን ልጅ</u> <u>ክቡርነትና ዋጋ ማሳነስና</u> ዝቅ አድርጎ መመልከትን አመላካች ነው። ሰው በሰውነቱ ብቻ ክቡር ነው። እንደ ብሌን ዓይነት በተጓደለ ቤተሰብና የወላጆችን ፍቅር ሳያገኙ የሚያድጉ፣ የሰቀቀን ሕይወት የሚገፉና የሰቀቀን ጩኸት የሚያሰሙ ሕጻናት ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ አሉንና፣ ቢያንስ ጩኸታቸውን ልናስተጋባ ይጠበቅብናል። የታሰሩ የፖለቲካ እሥረኞች በሙሉ ይፈቱ! እሥር ቤቶች በሙሉ ፈራርሰው ወደ ት/ቤት ይቀየሩ! ሕጻናትና ልጆች ያለወላጅ ማደግ አይገባቸውም ብለን፣ ደጋግመን ልንጮህና እሪታቸውን ልናዳምጥ ይገባል። የልጆች የሰቀቀን ጩኸት መቆም አለበት። የልጆች የሲቃ ልቅሶ መድረቅ አለበት፣ የልጆች የልብ ስብራት መጠገን አለበት። የብሌንን የሰቀቀን ጩኸትና የሰቀቀን ሕይወት እስቲ በአብዲ አብዱላሂ ድንቅ አባባል ልቋጨው።

"ጭካኔ ሳይሆን ፍቅር የሰውን ልብ ይማርካል"

አብዲ አብዱላሒ (ያልታደለ ትውልድ) ከሚለው መጽሐፉ የተወሰደ

የሕዝብ ድምጽ ይከበር!
የታሰሩ የፖለቲካ እሥረኞች በሙሉ ያለ ቅድመ ሁኔታ ይፈቱ!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!
ቸር ይግጠመን